**ETIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT GUARD**

# *ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ በወቅታዊ የሃገራችን ጉዳይ ላይ የተሠጠ የአቋም መግለጫ*

*ይህ ወንጀለኛ ቡድን በአሁኑ ሥዓት ለም የእርሻ መሬታችን ለባዕዳን አሳልፎ በመስጠት ላይ ይገኛል:*

እንደሚታወቀው እ.ኤ.አ. በ1991 ዓ.ም. በአለም ላይ የሶሻሊስቱ ዓለም /Socialist bloc/ መፍረክረክ በኢትዮጵያ የነበረውን አምባገነን ወታደራዊ መንግስት ከስልጣኑ ለመውደቅ ጉልህ ሚና የተጫወተ ቢሆንም በወቅቱ መሳሪያ አንስተው ይፋለሙ ከነበሩት ሃይሎች መካከል ወያኔ መራሹ ቡድን በተፈጠረው የሃይል ክፍተት /Power vacuum/ በመጠቀም ወደሥልጣን መምጣቱ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ ይህ ቡድን ገና ከመጀመሪያው የዘውጌ ፖለቲካን /Ethnic Politics/ በማቀንቀን ከ76 በላይ ብሄሮች እና ብሄረሰቦች የሚኖሩባትን ሃገር በዘር፤በቋንቋ እና በጎሳ በመከፋፈል የሃገሪቱን አንድነት አደጋ ላይ ከመጣሉም ባሻገር የ80 ሚሊዮን ህዝብ መኖሪያ የሆነችውን ሃገር "ወደብ ሸቀጥ ነው" በሚል ፈሊጥ የባህር በር አልባ አድርጓታል።ከዚህም ባሻገር ከጎረቤት ሃገር ኤርትራ ጋር በነበረው ሃገራዊ ጥቅምን ያላማከለ ግንኙነት መሰረት በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን እልቂት ምክንያት ወደ ሆነ ጦርነት ሃገራችንን መማገዱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በሌላ በኩል በውጭው አለም ተቀባይነትን /External Legitimacy/ ለማግኘት ሲል ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ገንብቻለሁ ቢልም "ህገ-መንግስቱም" ይሁን "ህገ-መንግስታዊው ስርዓት" የገዥውን መደብ ጥቅም ከማስጠበቅ በዘለለ በሃገራችን ዘላቂ ሰላም፤ፍትህ፤የዜጎች እኩልነት፤ሁሉንም ተጠቃሚ ያደረገ የሃብት ክፍፍል፤ዜጎች በሃገሪቱ የትኛውም ክፍል ተዘዋውረው የመስራት እና የመኖር መብታቸውን ያላረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በየጊዜው በሚወጡ አፋኝ ህጎች መሰረት ዜጎቻችን ለእስር፤ለስደት እና ለሞት ተዳርገዋል።

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት መግለጽ የማይችሉበት፤የሃገሪቱ ሃብት ጥቂት በሚባሉ የስርዓቱ ጥቅመኞች መዳፍ ስር የወደቀበት፤የህግ ስርአቱ ለፍትህ ከመቆም እና ህዝብን ከማገልገል ይልቅ የገዥው መደብ የፖለቲካ መሳሪያ የሆነበት፤የሃገሪቱ የመከላከያ እና የደህንነት ተቋማት ታማኝነታቸው ከሃገር እና ህዝብ ይልቅ ለገዥው መደብ የሆነበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

ይህ አፋኝ መደብ በሃገሪቱ ተቋማዊ አስተዳደር /Institutional administration/ ከመገንባት ይልቅ በግለሰብ ፖለቲካዊ ስብዕና ዙሪያ /On the epicentre of individual/ የተገነባ በመሆኑ የአገዛዙ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ቀሪው የስርዓቱ ርዝራዥ በመቀበሪያው ጉድጓድ አፋፍ ላይ ይገኛል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር*ዘብ* በወቅታዊ የሃገራችን ጉዳይ ላይ የደረሰበትን አቋም ከዚህ ቀጥሎ ያቀርባል።

1. የወያኔ ስርዓት ቀሪ ርዝራዦች አንዳንድ ጥገናዊ ለውጥ በማድረግ ማለትም የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት እና መሰል ተግባራትን በማድረግ ከውስጥ እና ከውጭ ድጋፍ በማሰባሰብ የአስከፊውን ስርአት ዕድሜ ለማራዘም የሚደርጉትን ጥረት ከወዲሁ የማንቀበለው ሲሆን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር በጥገናዊ ለውጥ መፍትሄ እንደማያገኝ ለማሳወቅ እንወዳለን።ይህ ወያኔ/ኢህአዴግ አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ የሚጠቀምበት የማደናገሪያ ስልት በሃገራችን ለተንሰራፋው ዘርፈ ብዙ የማህበራዊ፡ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መልስ የማይሰጥ ይልቁንም የገዥውን ስርዓት ዕድሜ ከማራዘም የዘለለ ሃገራዊ ፋይዳ የሌለው እርምጃ ነው።

2. የኢትዮጵያ የፖለቲካ፡ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍትሄ የሚያገኙት ሁሉን አቀፍ እና አሳታፊ በሆነ ስር-ነቀል የሽግግር ሂደት መሆኑን በመገንዘብ ይህ አመለካከት ካላቸው ሃይሎች እና ይህን መድረክ እያመቻቹ ካሉ አካላት ጋር በቅርብ ለመስራት እንቅስቃሴ የጀመርን ሲሆን በየደረጃው የምንደርስበትን በተከታታይ የምናሳውቅ ይሆናል።

3. ሃገራችን ኢትዮጵያ ከምትገኝበት ጂኦግራፊካል አቀማመጥ አንፃር እናም የቀጠናው ያለመረጋጋት አሁን ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር ተደማምሮ ሃገሪቱን እና ህዝቦቿን ለጥፋት ሃይሎች አሳልፎ እንዳይሰጥ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የማያሻማ አቋም ያላቸው አካላት በሙሉ ከጎናችን በመሰለፍ ለሽግግር ሂደቱ የበኩላቸውን ገንቢ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

4. መላው የሃገራችን ህዝቦች ሰብዐዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ተገፎ በግፍ እና በሰቆቃ ኑሯቸውን የሚገፉበት ጊዜ የሚያበቃበት፡እንዲሁም የጥቂት ጎሩያነ-ምስፍና /Minorities Supermacism/ የጭቆና ቀምበርን ከላያቸው ላይ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ አሽቀንጥረው የሚጥሉበት ታሪካዊ ወቅት ላይ መሆናቸውን በመገንዘብ አፋኙን ስርአት “በቃ” እንዲሉት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

-ወገን ልብ በሉ : ? መብቱ ሲረገጥ ያቀረቀር ሞቶ ያልተቀበር:

***ሁሉም ለናት አገሩ ዘብ ይቁም !!!የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር-ዘብ ፍራንክፈርት /ጀርመን-09/January-2014***

***www.eppfguard.com***

***Face book ;guard eppfg***

***Tel:+4915785069477***